**በጉለሌ ክፍለ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት**

**የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ሞዴል ፈተና**

**ሒሳብ ጥር 2018 ዓ.ም "Jan 2026"**

**የጥያቄዎች ብዛት፦ 30** **የተፈቀደው ሰዓት፦ 1 ሰዓት**

**አጠቃላይ መመሪያዎች**

ይህ የሒሳብ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 30 ጥያቄዎች ተካተዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነው አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተናው ላይ የተሰጡትን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው ለብቻ በተዘጋጀው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው፤ በመልስ መስጫው ላይ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር የሚመለስ ሲሆን የሚሰራው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛው መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈልግ በፊት የጠቆረውንበደንብ በማጥፋት መፅዳት አለበት፡፡

መልስ የሚሰጠው በመልስ መስጫው ላይ ብቻ ነው ለምሳሌ መልሳቹ **ለ** ከሆነ ከታች በሚታየው መልክ ማጥቆር አለባችሁ

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ○ | ● | ○ | ○ |

ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተፈቀደውን ሰዓት 1 ሰዓ ነው፡፡ ፈተናውን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠው ሰዓት ሲያበቃ ለመስረያነት የምንጠቀምበትን መፃፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናውን መስራት ማቆም አለብን ፡፡ፈተናው እንት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኝዋ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዓ የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም ፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባቸው መረጃዎች በሙሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መስራት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡**

LIVEWORKSHEETS

**ትዕዛዝ፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አራት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀት ላይ አጥቁር/ሪ።**

1. ርዝመቱ 7ሜ የሆነ ካሬ ስፋት ስንት ነው?

   ሀ. 7ሜ $^2$ ሐ. 49ሜ$^2$

   ለ. 14ሜ $^2$ መ. 21ሜ $^2$

2. ከሚከተሉት ውስጥ ዝቅተኛ የቆዳ ስፋት መለኪያ ምድብ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሚሊሜትር ካሬ ሐ. ሜትር ካሬ

   ለ. ሴንቲ ሜትር ካሬ መ. ኪሎ ሜትር ካሬ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የፈሳሽ ቁሶች መለኪያ ምድብ አሃድ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሊትር ሐ. ኩንታል

   ለ. ግራም መ. ኪሎ ግራም

4. የአንድ ሬክታንግላዊ ጠረጴዛ የላይኛው ገጽ ስፋት 3 ሜ$^2$ ቢሆን የዚህ ጠረጴዛ ስፋት በሴ.ሜ$^2$ ስንት ይሆናል?

   ሀ. 20,000 ሴ.ሜ$^2$ ሐ. 10,000 ሴ.ሜ$^2$

   ለ. 30,000 ሴ.ሜ$^2$ መ. 3,000 ሴ.ሜ$^2$

5. የአንድ ሬክታንግላዊ ቅርጽ ያለው ሳጥን ርዝመት 4ሜ፣ ወርድ 2ሜ እና ከፍታው 10ሜ ቢሆን የሳጥኑ ይዘት ስንት ይሆናል?

   ሀ. 80ሜ$^2$ ሐ. 8ሜ$^2$

   ለ. 8ሜ$^3$ መ. 80ሜ$^3$

6. ከሚከተሉት ውስጥ ህገኛ ክፍልፋይ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. $\frac{2}{3}$ ሐ. $2\frac{5}{7}$

   ለ. $\frac{100}{100}$ መ. $\frac{7}{14}$

7. የስሌት $\frac{3}{2}+\frac{4}{5}$ ውጤት ስንት ነው?

   ሀ. $\frac{7}{10}$ ሐ. $\frac{19}{10}$

   ለ. $\frac{11}{10}$ መ. $\frac{23}{10}$

8. ከሚከተሉት ውስጥ የ2.070+10.806 ትክክለኛ ውጤት የቱ ነው

   ሀ. 12.786 ሐ. 12.678

   ለ. 12.867 መ. 12.876

LIVEWORKSHEETS

9. የአንድ ትምህርት ቤት ህንፃ 20.25 ሜትር ቁመት ከፍታ አለው። ከዚህ ህንፃ ቀጥሎ ያለ ሌላ ህንፃ ደግሞ 26.75 ሜትር ቁመት ከፍታ ቢኖረው፣ ሁለተኛው ህንፃ ከመጀመሪያው ህንፃ በስንት ይበልጣል?

ሀ. 6.2 ሜትር　　　ሐ. 6.4 ሜትር

ለ. 6.5 ሜትር　　　መ. 6.7 ሜትር

10. የ ስሌት $\frac{9}{5}$ + 0.3 ድምር ውጤት ስንት ይሆናል?

ሀ. 2.5　　　ሐ. 1.2

ለ. 2.3　　　መ. 2.1

11. የ $12\frac{5}{8}$ - 1.75 ስሌት ትክክለኛ ውጤት የቱ ነው?

ሀ. $\frac{449}{20}$　　　ሐ. $\frac{449}{10}$

ለ. $\frac{449}{40}$　　　መ. $\frac{87}{8}$

12. ከሚከተሉት ውስጥ የ$1.008 \times 1000$ ትክክለኛው ውጤት የትኛው ነው?

ሀ. 10.08　　　ሐ. 1008

ለ. 1.008　　　መ. 100.8

13. ከሚከተሉት ውስጥ የ $\frac{2}{5} \times 1.25$ ትክክለኛ ውጤት የቱ ነው?

ሀ. 0.5　　　ሐ. 0.25

ለ. 0.4　　　መ. 0.3

14. የ 5 ኪሎ ግራም ስኳር ዋጋ 155.50 ብር ቢሆን፣ የአንድ ኪሎ ግራም ስኳር ዋጋ ስንት ነው?

ሀ. 31.10 ብር　　　ሐ. 30 ብር

ለ. 31 ብር　　　መ. 30.10 ብር

15. ከሚከተሉት ውስጥ $25\frac{1}{2} \div 4.\frac{1}{2}$ ትክክለኛ ውጤት የቱ ነው?

ሀ. 6　　　ሐ. $\frac{51}{9}$

ለ. $\frac{17}{4}$　　　መ. $\frac{51}{17}$

16. ለማለዳ የእግር ጉዞ ሶስት ሰዎች አብረው ይሄዳሉ። የእርምጃቸው መጠን 75 ሴ.ሜ፣ 80 ሴ.ሜ እና 90 ሴ.ሜ ነው። ሁሉም ተጓዦች ተመሳሳይ ርቀት መሄዳቸውን ለማረጋገጥ እያንዳንዳቸው በእግር መጓዝ ያለባቸው ዝቅተኛው ርቀት ምን ያህል ነው?

ሀ. 3200 ሴ.ሜ　　　ሐ. 3000 ሴ.ሜ

ለ. 3500 ሴ.ሜ　　　መ. 3600 ሴ.ሜ

LIVEWORKSHEETS

17. የ $\frac{11}{12}$ ዝቅተኛ የሂሳባዊ ቃል  የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{1}{12}$ ሐ. $\frac{11}{1}$

ለ. $\frac{11}{12}$ መ. $\frac{12}{11}$

18. የ ክፍልፋይ $\frac{678}{10000}$ ትክክለኛው አስርዮሽ የቱ ነው?

ሀ. 0.678 ሐ. 0.00678

ለ. 0.0678 መ. 0.6780

19. የአስርዮሽ ቁጥር 0.00067 ትክክለኛው ክፍልፋይ የቱ ነው?

ሀ. $\frac{67}{100000}$ ሐ.$\frac{67}{1000}$

ለ. $\frac{67}{10000}$ መ. $\frac{67}{100}$

20. የ 0.45% ትክክለኛው ክፍልፋይ የቱ ነው?

ሀ. $\frac{100}{45}$ ሐ. $\frac{15}{100}$

ለ. $\frac{100}{15}$ መ. $\frac{45}{100}$

21. የመቶኛ 25% ትክክለኛው ክፍልፋይ የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{1}{2}$ ሐ. $\frac{1}{3}$

ለ. $\frac{1}{4}$ መ. $\frac{1}{5}$

22. ማርታ ለልደቷ 120 ግራም ኬክ ገዛች ለተቀሩት 3 ጓደኞቿ 11 ግ፣ 23 ግ እና 32 ግ ኬክ በግምት ብታከፋፍል የቀረው የኬክ መጠን በመቶኛ ስንት ነው?

ሀ. 67% ሐ. 66%

ለ. 65% መ. 45%

23. በአንድ ትምህርት ቤት የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ወንዶች 78 እና ሴቶች ደግሞ 92 ቢሆኑ የወንድ ተማሪዎች በመቶኛ ስንት ነው?

ሀ. 54.12% ሐ. 45%

ለ. 45.88% መ. 54%

24. ከሚከተሉት አገላለጾች ውስጥ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. $\frac{1}{0} = 0.5$ ሐ. $\frac{4}{10} = 0.2$

ለ. $\frac{5}{100} = 0.04$ መ. $\frac{1}{4} = 0.25$

LIVEWORKSHEETS

25. ከሚከተሉት ክፍልፋዮች ውስጥ **ከትንሽ ወደ ትልቅ** በቅደም ተከተል የተቀመጠው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{7}{8}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{3}{5}$ ፣ $\frac{1}{2}$ ሐ. $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{7}{8}$ ፣ $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{3}{5}$

ለ. $\frac{3}{5}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{7}{8}$ መ. $\frac{1}{2}$ ፣ $\frac{3}{5}$ ፣ $\frac{3}{4}$ ፣ $\frac{7}{8}$

26. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ **ተጋማሽ** ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. 320 ሐ. 1,765

ለ. 2,372 መ. 124

27. ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ለ 9 ተካፋይ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 450 ሐ. 541

ለ. 451 መ. 150

28. የ 72 እና 36 **ትልቁ የጋራ አካፋይ** የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. 9 ሐ. 72

ለ. 18 መ. 36

29. ከሚከተሉት ውስጥ ትንሹ የጋራ ብዜት ት.ጋ.ብ (20 ፣ 30) የትኛው ነው?

ሀ. 20 ሐ. 30

ለ. 60 መ. 25

30. ከሚከተሉት ውስጥ የትንሹ ባለ አራት አሃዝ ሙሉ ቁጥር **ብቸኛ ትንትን** የቱ ነው?

ሀ. $2^2 \times 3^2$ ሐ. $2^2 \times 5^2$

ለ. $2^3 \times 5^3$ መ. $2^3 \times 3^2$

LIVEWORKSHEETS